







# USCIS ስደተኞች እና ጥገኞችን እንኳን ደህና መጣችሁ ይላል

U.S. Citizenship and Immigration Services

M-1186-AMH (9/20)

# USCIS ስደተኞች እና ጥገኞችን እንኳን ደህና መጣችሁ ይላል

U.S. Citizenship
and Immigration
Services

# USCIS ስደተኞች እና ጥገኞችን እንኳን ደህና መጣችሁ ይላል

የዩ.ኤስ. ዲፓርትመንት ኦፍ ሆምላንድ ሴኩሪቲ (DHS) ክፍል የሆነዉ፣ ዩ.ኤስ. ዜግነት እና ኢሚግሬሽን አገልግሎቶች (USCIS)፣ እርስዎ እንደ ስደተኛ ወይም ጥገኛ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ሲመጡ እንኳን ደህና መጡ ብሎ ይቀበልዎታል፡፡ እኛ ለእርስዎ ክህሎቶች እና ተሰጦዎች ዋጋ እንሰጣለን፣ እና እርስዎ ወደ ማህበረሰብዎ ተቀላቅለዉ የተረጋጋ ሕይወት መምራት እና በዩናይትድ ስቴትስ ዉስጥ ስኬታማ መሆን እንዲችሉ እገዛ ማድረግ እንፈልጋለን፡፡ እንዲሁም እኛ እርስዎ የዩ.ኤስ. ዜጋ መሆን እንዴት መሆን እንደሚችሉ የሚያስረዳዎት መረጃዎችን ማካፈል እንፈልጋለን፡፡

ይህ ብሮሸር እርስዎ በዩናይትድ ስቴትስ ዉስጥ የተረጋጋ ሕይወትዎን መምራት እንዲችሉ እና ከዩ.ኤስ. ዜግነት ስለሚገኙ መብቶች፣ ሀላፊነቶች፣ እና ጥቅሞች ማወቅ እንዲችሉ ይረዳዎታል፡፡ የዩ.ኤስ. ዜጋ መሆን እርስዎ እንደ ሁሉም አሜሪካዊ ዜጎች ተመሳሳይ መብት ያጎናጽፎታል እና ለእርስዎ እና በእርስዎ አካባቢ ላሉ ዜጎች የጋራ የሆነ ባለቤትነት ስሜት እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡

## መብቶች እና ሀላፊነቶች

በዩናይትድ ስቴትስ ዉስጥ እንደሚኖር ስደተኛ ወይም ጥገኛ፣ እርስዎ በርካታ መብቶች አልዎት፣ ማለትም እዚህ ሀገር ዉስጥ እንደሚኖሩ ሌሎች ሰዎች ተመሳሳይ መብቶች አልዎት፡፡ ከእነዚህ መብቶች መካከል ጥቂቶቹ የመናገር ነጻነት፣ የሀይማኖት ነጻነት፣ እና የመሰብሰብ ነጻነትን ያካትታሉ፡፡




እርስዎ ሀላፊነቶችም አለብዎት፡፡ በዩናይትድ ስቴትስ ዉስጥ፣ እያንዳንዱ ሰዉ ሕግን ማክበር አለበት፡፡ እነዚህ ሕጎች እርሰዎ ቀደም ብለዉ ከኖሩባቸዉ ሌሎች ቦታዎች የተለዩ ሊሆኑ ስለሚችሉ የዩ.ኤስ. ሕጎችን መረዳት አለብዎት፡፡ ስለ አሜሪካ ታሪክ፣ መንግስት፣ እና ባህል ማወቅዎ ሀገርዎ ላይ እየኖሩ እንደሆነ ስሜት እንዲያድርቦት እገዛ ያደርጋል፡፡

**እርስዎ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት መብቶች አልዎት:**

- በዩናይትድ ስቴትስ ዉስጥ የትኛዉም ቦታ ላይ መኖር
- በዩናይትድ ስቴትስ ዉስጥ ስራ መስራት
- በተወሰኑ መስፈርቶች ላይ በመመስረት ዩናይትድ ስቴትስን ለቆ መዉጣት ወይም መመለስ
- እስከተወሰነ እድሜ ክልል ድረስ የሕዝብ ትምህርትን መከታተል፣ በግዛቱ ሕጎች ላይ በመመስረት
- ገደብ ለማይጣልበት የሶሻል ሴኩሪቲ ካርድ ማመልከቻ ማስገባት
- እርስዎ በሚገኙበት ግዛት ወይም ክልል ዉስጥ ለመንጃ ፍቃድ ወይም ሌላ አይነት የመንግስት መታወቂያ ማመልከቻ ማስገባት
- እርስዎ ብቁ የሚሆኑበት እድሜ ደረጃ ላይ ሲደርሱ ለሕጋዊ ቋሚ ነዋሪነት እና የዩ.ኤስ. ዜጋ ለመሆን ማመልከቻ ማስገባት

- የእርስዎ የትዳር አጋር ወይም ትዳር ያልያዙ ልጆች በዩናይትድ ስቴትስ ዉስጥ መኖር እንዲችሉ የጥገኝነት ወይም ከስደተኛዉ ጋር ዝምድና ያላቸዉ ሁኔታ ማግኘት እንዲችሉ ጥያቄ ማቅረብ
- ወንጀሎች ወይም በደልን ለሕግ አስከባሪዎች ማሳወቅ እና የእነርሱን እርዳታ ማግኘት

**እርስዎ ሀላፊነት አለብዎት እና ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን እንዲያደርጉ ይጠበቅቦታል:**

- ወደ ሌላ ሀገር ከመሄድዎ በፊት ለስደተኛ ጉዞ ሰነድ ማመልከቻ በማስገባት ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ለመመለስ ፍቃድ መጠየቅ፣ ጥገኛ ሁኔታን ያገኙ ቢሆንም
- ለሁሉም የፌደራል፣ የግዛት፣ እና አካባቢ ሕጎች ተገዢ መሆን
- የፌደራል፣ የግዛት እና የአካባቢ ታክሶችን መክፈል፣ የሚኖር ከሆነ
- እርስዎ ከ 18 እና 26 ዓመት እድሜ ክልል ዉስጥ የሚገኙ ወንድ ከሆኑ ለተለየ አገልግሎቶች ምዝገባ ማድረግ
- የመገኛ አድራሻ ለዉጥ ሲያደርጉ ከ 10 ቀናት በላይ ሳያልፍ ስለ አዲሱ መገኛዎ ለ USCIS ማሳወቅ
- ለአቅመ አዳም ያልደረሱ ልጅዎችዎን ወደ ትምህርት ቤት መላክ
- እርስዎ ስደተኛ ከሆኑ በዩናይትድ ስቴትስ ዉስጥ 1 ዓመት ከቆዩ በሗላ ለሕጋዊ ቋሚ ነዋሪነት ሁኔታ ማመልከቻ ማስገባት

## በዩናይትድ ስቴትስ ዉስጥ የተረጋጋ ሕይወትን መምራት

በዩናይትድ ስቴትስ ዉስጥ፣ እርስዎ የተረጋጋ ሕይወት መምራት እንዲችሉ እያንዳንዱ የመንግስት ደረጃ የተለያዩ ሚናዎችን ይጫወታል፡፡ በእርስዎ የሰፈራ ምደባ ሂደት ላይ ከአካባቢ፣ ከግዛት ፣ እና ከፌደራል መንግስት ቢሮዎች ጋር ሊገናኙ ይችላል፡፡



እርስዎ ወደ ተገቢዉ የመንግስት እገዛ ፕሮግራም መሄድ እንዲችሉ ለማገዝ ከስደተኞች ጋር የሚሰራ የእርስዎን የግዛቱ ስደተኛ አስተባባሪ፣ የግዛቱ ስደተኛ የጤና አስተባባሪ፣ የሰፈራ ምደባ ኤጀንሲ ወይም የአካባቢዉ ማህበረሰብ-ላይ የተመሰረተ ድርጅትን ያግኙ፡፡ በርካታ የመንግስት እገዛ ፕሮግራሞች በጊዜ-የተገደበ ለአገልግሎት ብቁ መሆን ጊዜ ቆይታዎች አሉዋቸዉ ይህም እርስዎ ጥገኝነት ሁኔታ ከተሰጥዎት ወይም ስደተኛ ሆነዉ እንዲገቡ ከተፈቀደሎት ጊዜ አንስቶ የሚጀምር ነዉ፡፡

እርስዎ እንግሊዝኛ ቋንቋን ለመማር እገዛ የሚፈልጉ ከሆነ፣ ለእንግሊዝኛ ቋንቋ የትምህርት ክፍል ምዝገባ ማድረግ ይችላሉ፡፡ ስለ እንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍሎች እና ሌሎች ትምህርት ክፍሎች እና አገልግሎቶች መረጃ ለማግኘት የእርስዎን የሰፈራ ምደባ ኤጀንሲ፣ የሕዝብ ላይብረሪ፣ የማህበራዊ አገልግሎት ኤጀንሲ፣ ወይም የፀሎት ቦታዎችን ይጠይቁ፡፡

## በእርስዎ ኢሚግሬሽን ሂደት ላይ ቀጣዮቹ ደረጃዎች

እርስዎ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ እንደ ስደተኛ ሆነዉ የገቡት ባለፉት 2 ዓመቶች ዉስጥ ከሆነ ወይም ባለፉት 2 ዓመቶች ዉስጥ የጥገኛ ሁኔታ የተሰጥዎት ከሆነ፣ የተወሰኑ የቤተሰብ አባላቶችዎ ከእርስዎ ጋር እዚህ መቀላቀል እንዲችሉ አቤቱታ ማቅረብ ይችሉ ይሆናል፡፡ ከዚህ በታች ለተጠቀሱት የቤተሰብ አባላቶችዎ አቤቱታ ማቅረብ ይችሉ ይሆናል:

- ትዳር አጋር
- ልጅ (ያላገባ/ያላገባች እና ለጥገኝነት ወይም ስደተኛ ሁኔታ ማመልከቻ ባስገቡበት ወቅት ከ 21 ዓመት በታች ለሆነ/ሆነች)

እርስዎ ቅጽ I-730፣ ስደተኛ/ጥገኛ ዘመድ አቤቱታን ለ USCIS ማቅረብ አለብዎት፣ ይህም መሆን ያለበት ጥገኝነት ከተሰጥዎት ወይም እንደ ስደተኛ ሆነዉ እንዲገቡ ከተፈቀደልዎት ጊዜ አንስቶ ባሉት 2 ዓመታቶች ዉስጥ ነዉ፣ ወይም የሰብዓዊነት ምክንያቶችን በማስረጃ በማሳየት የ 2-ዓመት ጊዜ ቆይታዉን እንዲያራዝሙ ይፈለጋል፡፡ ይህ ቅጽ እዚህ ጋር ይገኛል uscis.gov/i-730.

## ሕጋዊ ቋሚ ነዋሪነት

ሕጋዊ ቋሚ ነዋሪ (ግሪን ካርድ ያለዉ) ማለት በዩናይትድ ስቴትስ ዉስጥ ቋሚ በሆነ መልኩ ለመኖር እና ስራ ለመስራት ፍቃድ የተሰጠዉ/የተሰጣት ግለሰብ ማለት ነዉ፡፡ ለዚህ ሁኔታ ማረጋገጫነት፣ ግለሰቡ/ግለሰቧ ቋሚ ነዋሪነት ካርድ ይሰጠዋል/ይሰጣታል፣ ይህም በመደበኝነት ግሪን ካርድ በመባል ይታወቃል፡፡ እንዲሁም ግሪን ካርድን ማግኘት ግለሰቡ/ግለሰቧ ሙሉ ለሆነ የዩ.ኤስ. ዜግነት ማመልከቻ ለማስገባት ወደ የሚያስችል መንገድ ይመራዋል/ይመራታል (በዚህ ጉዳይ ላይ ከታች ተጨማሪ መረጃ ቀርቧል)፡፡

- ስደተኞች ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ከመጡበት ጊዜ አንስቶ ከሚኖረዉ 1 ዓመት በኋላ **የግዴታ** ለቋሚ ነዋሪነት ካርድ ማመልከቻ ማስገባት አለባቸዉ፡፡ ስደተኞች ይህን ማመልከቻ በሚያስገቡበት ወቅት በዩናይትድ ስቴትስ ዉስጥ ለ 1 ዓመት በአካል መኖራቸዉ ግዴታ ነዉ፡፡
- ጥገኞች ጥገኝነት ከተሰጣቸዉ ከ 1 ዓመት በኋላ ለቋሚ ነዋሪነት ካርድ **ምናልባት** ማመልከቻ ማስገባት ይችሉ ይሆናል፡፡ ጥገኞች ይህን ማመልከቻ በሚያስገቡበት ወቅት እንደ ጥገኛ በዩናይትድ ስቴትስ ዉስጥ ለ 1 ዓመት በአካል መኖራቸዉ ግዴታ ነዉ፡፡

ለሕጋዊ ቋሚ ነዋሪነት ሁኔታ ማመልከቻ ለማስገባት እና ቋሚ የነዋሪነት ካርድ ለማግኘት፣ ቅጽ I-485 ፣ ቋሚ ነዋሪነትን ማስመዝገቢያ ወይም ሁኔታዉን

ማስተካከያ ማመልከቻን ያስገቡ፡፡ ይህ ቅጽ እዚህ ጋር ይገኛል uscis.gov/i-485. ምንም እንኳን ቅጽ I-485 ማመልከቻን ለማስገባት ለጥገኞች ክፍያ ቢኖረዉም፣ ቅጽ I-485 ማመልከቻን ለማስገባት ለስደተኞች ምንም አይነት ክፍያ የለዉም፡፡ ማህበረሰብ-ላይ የተመሰረቱ ድርጅቶች፣ ይህም የእርስዎ አካባቢ ሰፈራ ምደባ ኤጀንሲን ያካትታል፣ በዚህ ሂደት ላይ ለእርስዎ እገዛ ሊያደርጉልዎት ይችላሉ፡፡

## ስደተኞች

እርስዎ ስደተኛ ከሆኑ፣ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ዉስጥ እንደ ስደተኛ ሆነዉ እንዲገቡ ከተፈቀደልዎት ጊዜ አንስቶ ባለዉ 1 ዓመት ዉስጥ በሕግ መሰረት ለሕጋዊ ቋሚ ነዋሪነት ሁኔታ ማመልከቻ እንዲያስገቡ ይፈለጋል፡፡

**ለሕጋዊ  ቋሚ ነዋሪነት ማመልከቻ ያስገቡ**

**ቅጽ I-485 ፣ ቋሚ ነዋሪነትን ለማስመዝገብ ወይም ሁኔታዉን ማስተካከያ ማመልከቻ ማመልከቻ ያስገቡ፡፡ ስደተኞች ቅጽ I-485 ማመልከቻን ለማስገባት ወይም ባዮሜትሪክ አገልግሎቶችን ለማግኘት ክፍያ አይፈጽሙም፡፡**

**እርስዎ ማመልከቻ ለማስገባት ብቁ ሊሆኑ የሚችሉት:**

- እንደ ስደተኛ ሆነዉ እንዲገቡ ከተፈቀደልዎት ጊዜ አንስቶ በዩናይትድ ስቴትስ ዉስጥ ቢያንስ ከ 1 ዓመት በላይ በአካል የኖሩ ከሆነ፤
- የእርስዎን ቅጽ I-485 ማመልከቻን በሚያስገቡበት ጊዜ ላይ በዩናይትድ ስቴትስ ዉስጥ በአካል የሚገኙ ከሆነ፤
- እንደ ስደተኛ ሆነዉ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ እንዲገቡ ሊፈቀድልዎት የሚችሉ ከሆነ፤ እና
- የእርስዎን የስደተኛ ሁኔታ እንዲቋረጥ ያላደረጉ ከሆነ፡፡

**ለበለጠ መረጃ** uscis.gov/i-485 **እና** uscis.gov/greencard/refugees **ይጎብኙ ፡፡**

## ስደተኞች

**ለዩ.ኤስ. ዜግነት ማመልከቻ ያስገቡ**

እርስዎ ለተወሰኑ በቁጥር የሚጠቀሱ ዓመታቶች ሕጋዊ ቋሚ ነዋሪ የነበሩ ከሆነ እና ሌሎች የብቁነት መስፈርቶችን የሚያሟሉ ከሆነ ለኒዉትራላይዜሽን ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ እባክዎትን ለበለጠ መረጃ uscis.gov/citizenship ይጎብኙ፡፡

## ጥገኞች

**እርስዎ ጥገኛ ከሆኑ፣ እርስዎ ለጊዜ ቆይታዉ በሙሉ ነዋሪነትዎን ጠብቀዉ የቆዩ ከሆነ፣ ለሕጋዊ ቋሚ ነዋሪነት ሁኔታ ጥገኝነት ከተፈቀደልዎት በኋላ ባለዉ 1 ዓመት ዉስጥ ማመልከቻ ለማስገባት ብቁ ይሆናሉ፣ ነገር ግን ማመልከቻ እንዲያስገቡ አይገደዱም፡፡**

**ለሕጋዊ ቋሚ ነዋሪነት ማመልከቻ ያስገቡ**

ቅጽ I-485 ፣ ቋሚ ነዋሪነት ለማስመዝገብ ወይም ሁኔታዉን ማስተካከያ ማመልከቻን ያስገቡ፣ እና ተገቢ የሆኑትን የማመልከቻ እና ባዮሜትሪክ አገልግሎት ክፍያዎችን ይፈጽሙ፡፡

እርስዎ ማመልከቻ ለማስገባት ብቁ ሊሆኑ የሚችሉት:

- ጥገኝነት ሁኔታ ከተሰጥዎት ጊዜ አንስቶ ቢያንስ ለ 1 ዓመት በዩናይትድ ስቴትስ ዉስጥ በአካል የኖሩ ከሆነ ነዉ፤
- የእርስዎን ቅጽ I-485 ማመልከቻን በሚያስገቡበት ጊዜ ላይ በዩናይትድ ስቴትስ ዉስጥ በአካል የሚገኙ ከሆነ፤
- የስደተኛ ትርጓሜ መስፈርትን ማሟላት የሚቀጥሉ ከሆነ ወይም የስደተኛ ግለሰብ የትዳር አጋር ወይም ልጅ ከሆኑ፤
- በየትኛዉም የዉጪ ሀገር ዉስጥ በተረጋጋ መልኩ የሰፈራ ምደባ ያላገኙ ካልሆነ፤
- እንደ ስደተኛ ሆነዉ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ እንዲገቡ ሊፈቀድልዎት የሚችል ከሆነ፤ እና

## ጥገኞች

- የእርስዎን የጥገኛ ሁኔታ እንዲቋረጥ ያላደረጉ ከሆነ፡፡

ለበለጠ መረጃ uscis.gov/i-485 እና uscis.gov/greencard/asylees ይጎብኙ፡፡

**ለዩ.ኤስ. ዜግነት ማመልከቻ ያስገቡ**

እርስዎ ለተወሰኑ በቁጥር የሚጠቀሱ ዓመታቶች ሕጋዊ ቋሚ ነዋሪ የነበሩ ከሆነ እና ሌሎች የብቁነት መስፈርቶችን የሚያሟሉ ከሆነ ለኒዉትራላይዜሽን ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ እባክዎትን ለበለጠ መረጃ uscis.gov/citizenship ይጎብኙ፡፡

## ዜግነት

ዜግነት ሁሉኑንም አሜሪካዊያኖችን የሚያስተሳስር የጋራ ገመድ ነዉ፡፡ እኛ በዘር ወይም በሀይማኖት አንድ የሆንን ሀገር አይደለንም ነገር ግን የጋራ በሆኑ ነጻነት፣ ከሁሉም ሀይል ነጻ መሆን፣ እና እኩልነት የጋራ እሴቶች ላይ የተመሰረትን ሀገር ነን፡፡ የዩ.ኤስ. ዜጋ በመሆን፣ እርስዎ የእኛ ሀገር እንዴት መመራት እንዳለባት ሀሳብዎን የሚያቀርቡበት ድምጽ ይኖርዎታል፡፡

እንደ ሕጋዊ ቋሚ ነዋሪነትዎ እርስዎ የሚፈጽሟቸዉ ድርጊቶች በኋላ ላይ የዩ.ኤስ. ዜጋ መሆን የሚችሉበት ሁኔታ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡ የዩ.ኤስ. ዜጋ ለመሆን የሚካሄደዉ ሂደት ኒዉትራላይዜሽን በመባል ይታወቃል፡፡ እርስዎ እንደ ዩ.ኤስ. ዜጋ ሆነዉ የዜግነት መብት ለማግኘት ሁሉንም የብቁነት መስፈርቶች ማሟላት ይኖርቦታል፡፡



በአጠቃላይ፣ እንደ ሕጋዊ ቋሚ ነዋሪነት የተወሰኑ በቁጥር የሚጠቀሱ ዓመታቶችን ካስቆጠሩ በኋላ፣ እርስዎ ለኒዉትራላይዜሽን ማመልከቻ ማስገባት ይችላሉ። ስደተኞች እና ጥገኞች ለሕጋዊ ቋሚ ነዋሪነት ማመልከቻቸዉ ተቀባይነት ካገኘበት ቀን አንስቶ ካሉት 5 ዓመታቶች በኋላ ለኒዉትራላይዜሽን ማመልከቻ ማስገባት ይችላሉ። ጥገኞች ለሕጋዊ ቋሚ ነዋሪነት ሁኔታ የእነርሱ ቅጽ I-485 ከመጽደቁ ከ 1 ዓመት በፊት ተቀባይነት ያገኛል።  የእነርሱ ቅጽ I-485 ከጸደቀ በኋላ፣ ስደተኞች የሕጋዊ ቋሚ ነዋሪነት ሁኔታቸዉ ዩናይትድ ስቴትስ ከገቡበት ቀን ጀምሮ ተቀባይነት ያገኛል።

የኒዉትራላይዜሽን ብቁነት መስፈርቶች ዝርዝርን ለማግኘት፣ uscis.gov/citizenship ይጎብኙ። ከእነዚህ መስፈርቶች መካከል የተወሰኑት ከታች የተዘረዘሩትን ያካትታሉ:

- እርስዎ ለተወሰነ የጊዜ ቆይታ በዩናይትድ ስቴትስ ዉስጥ በአካል መገኘት ይኖርቦታል።
- እርስዎ በዩናይትድ ስትቴስ ዉስጥ ያልተቋረጠ የኑሮ ሁኔታ ሊኖርዎት ይገባል።
- እርስዎ ጥሩ የሆነ የሞራል ባህሪያቶች ሊኖርዎት ይገባል።
- እርስዎ መሰረታዊ የሆነ እንግሊዝኛ ቋንቋን መናገር፣ ማንበብ፣ መጻፍ፣ እና መረዳት አለብዎት እና ስለ ዩ.ኤስ. ታሪክ እና መንግስት (ሲቪክስ) ግንዛቤ ሊኖርዎት ይገባል።
- የዩ.ኤስ. ሕገ መንግስትን መርህዎች እና ሀሳቦች መደገፍ አለብዎት እና ለዩናይትድ ስቴትስ ታማኝነትዎን በመሃላ ለማረጋገጥ ፍቃደኛ መሆን አለብዎት።

ለኒዉትራላይዜሽን ማመልከቻ ለማስገባት፣ ቅጽ N-400 ፣ የኒዉትራላይዜሽን ማመልከቻን፣ አንላይን ላይ በ uscis.gov/n-400 ያስገቡ፡፡ እንዲሁም የቅጽ N-400 እና የእርስዎ ባዮሜትሪክ ክፍያን አንላይን ላይ መፈጸም ይችላሉ፡፡ ብቁ ለሆኑ ግለሰቦች የሚያስፈልጉት የኒዉትራላይዜሽን መስፈርቶች የማይካተቱ ሁኔታዎች እና ማሻሻያዎች ይኖራሉ፡፡ በተጨማሪም USCIS አካል ጉዳት ላለባቸዉ ግለሰቦችም እገዛ ይሰጣል፡፡ በርካታ የማህበረሰብ ድርጅቶች፣ ለምሳሌ የአካባቢ ሰፈራ ምደባ ኤጀንሲዎች፣ እርስዎ ለኒዉትራላይዜሽን ሂደት መዘጋጀት እንዲችሉ እገዛ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡



የዩ.ኤስ. ዜግነትን ከማግኘት ጋር ተያያዥ የተወሰኑ ጥቅማ ጥቅሞች፣ መብቶች፣ እና ሀላፊነቶች ይመጣሉ፣ እነዚህም በፌደራል ምርጫዎች ላይ መሳተፍ መቻል፣ በዳኝነት ሂደት ዉስጥ እንደ ፍርድ ሸንጎ ማገልገል፣ የዩ.ኤስ. ፓስፓርትን ይዞ ጉዞ ማድረግ፣ ለፌደራል ክፍት የስራ ቦታዎች መወዳደር፣ እና በሕዝብ የተመረጠ ባለስልጣን መሆን መቻልን ያካትታሉ፡፡

## USCIS ያግኙ

**ተጨማሪ መረጃዎች ለማግኘት፣ የእርስዎን ጉዳይ የደረሰበት ደረጃን ለማረጋገጥ፣ ወይም የ USCIS ቢሮን ለማግኘት uscis.gov ይጎብኙ፡፡ USCIS ከክፍያ ነጻ በሆነ ስልክ መስመር 800-375-5283 ደዉለዉ ማግኘት ይችላሉ፡፡ መስማት ለተሳናቸዉ ፣ ወይም መስማት ለሚያዳግታቸዉ ወይም የንግግር እክሎች ላሉባቸዉ ሰዎች፣ በ TTY 800-767-1833 መደወል ይቻላል፡፡ አገልግሎቱን በእግሊዝኛ እና ስፓኒሽ ቋንቋ ማግኘት ይችላሉ፡፡ እንዲሁም የ USCIS**

መገኛ ማዕከልን ለማግኘት uscis.gov/contactcenter መጎብኘት ይችላሉ።

## USCIS አቅርቦቶች

### የዩ.ኤስ. ሲትዝንሺፕ ኤንድ ኢሚግሬሽን ሰርቪስስ (USCIS)

USCIS ወደ ዩናይትድ ስቴትስ የሚደረግን ሕጋዊ ስደት በበላይነት ይቆጣጠራል። የግሪን ካርድ ማመልከቻ ማስገባት፣ የዩ.ኤስ. ዜግነት ለማግኘት ጥረት ማድረግ፣ ከቤተሰብ ጋር በድጋሚ መገናኘት፣ ወደ ሌላ ሀገር ጉዞ ለማድረግ ፍቃድ ማግኘት፣ እና ሌሎች ተጨማሪ ነገሮች እንዴት ማድረግ እንደሚችሉ ይማሩ።

### ለስደተኞች እና ጥገኞች አቅርቦቶች

uscis.gov/howdoi/refugeesasylees

### እንኳን ወደ ዩናይትድ ስቴትስ በደህና መጡ: ለአዲስ ስደተኞች መመሪያ

ይህ መመሪያ እርሰዎ እና የእርስዎ ቤተሰብ በዩናይትድ ስቴትስ ዉስጥ ለሚኖራችሁ የእለት ከእለት ሕይወት የሚያስፈልጉ መሰረታዊ መረጃዎችን ያስተዋዉቃል። የእርስዎን መብቶች እና ሀላፊነቶችን ይገልጻል፣ እርስዎ በአካባቢዎ በሚገኝ ማህበረሰብ እንቅስቃሴዎች ዉሰጥ ተሳትፎ ማድረግ የሚችሉበት ሁኔታ ላይ ሀሳቦችን ያቀርባል፣ እና ህጋዊ ቋሚ ነዋሪ ከሆኑ በኋላ ለዩ.ኤስ. ዜግነት ማመልከቻ የሚያስገቡበትን እቅድ እንዲያወጡ እገዛ ያደርግሎታል።

uscis.gov/newimmigrants

### በዩ.ኤስ. ዉስጥ የተረጋጋ ሕይወት መምራት

ይህ ድህረ ገጽ ስለ ዩናይትድ ስቴትስ፣ ትምህርት እና የልጅ እንክብካቤ፣ አደጋዎች እና ደህንነቶች፣ ከዩናይትድ ስቴትስ ዉጪ ጉዞ ማድረግ፣ ስራ ቅጥር፣ በዩናይትድ ስቴትስ ዉስጥ የተረጋጋ ሕይወት መምራት፣ የመንግስት ጥቅማ ጥቅሞች፣ የጤና እንክብካቤ፣ እና ገንዘብ እና ፋይናንስን የተመለከቱ መረጃዎችን ለእርስዎ ያቀርባል።

uscis.gov/tools/settling-us

## USCIS አቅርቦቶች

### የዜግነት አቅርቦት ማዕከል

ይህ ዌብሳይት እርስዎ ለዩ.ኤስ. ዜግነት ዝግጅት ማድረግ እንዲችሉ የሚረዱ ትምህርታዊ መሳሪያዎችን እና መረጃዎችን ያቀርባል፡፡

uscis.gov/citizenship

### እንዳይጭበረበሩ ይጠንቀቁ

እርስዎ በኢሚግሬሽን ጉዳዮች ላይ የሕግ ምክር የሚፈልጉ ከሆነ፣ ለእርስዎ እገዛ እያደረገ ያለዉ ግለሰብ የሕግ ምክር ለመስጠት ፍቃድ ያለዉ መሆኑን ያረጋግጡ፡፡ በዩ.ኤስ. ዲፓርትመንት ኦፍ ጀስቲስ የሚታወቅ ድርጅት ዉስጥ የሚሰራ/የምትሰራ ጠበቃ ወይም እዉቅና የተሰጠዉ/የተሰጣት ተወካይ ብቻ ለእርስዎ የሕግ ምክር መስጠት ይችላሉ፡፡

uscis.gov/avoid-scams

uscis.gov/avoid-scams/find-legal-services

### ቅጾች

**ቅጽ I-765** ለስራ ፍቃድ ማመልከቻ ለማስገባት፣ ፍቃድዎን ለማደስ፣ ወይም የእርስዎን ሰነድ ለመቀየር ይጠቀሙ፡፡

uscis.gov/i-765

**ቅጽ I-730** የትዳር አጋርዎን ወይም ልጆችዎን ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ለማምጣት ይጠቀሙ፡፡

uscis.gov/i-730

**ቅጽ I-131** የስደተኛ ጉዞ ሰነድን በመያዝ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ለመመለስ ጥያቄ ለማቅረብ ይጠቀሙ፡፡

uscis.gov/i-131

**ቅጽ I-485** እርስዎ በዩናይትድ ስቴትስ ዉስጥ የሚገኙ ከሆነ ለሕጋዊ ቋሚ ነዋሪነት ሁኔታ ማመልከቻ ለማስገባት ይጠቀሙ፡፡

uscis.gov/i-485

| USCIS አቅርቦቶች |
|---|
| **ቅጽ N-400** ለዩ.ኤስ. ዜግነት ማመልከቻ ለማስገባት ይጠቀሙ፡፡<br><br>uscis.gov/n-400<br><br>**ቅጽ AR-11** የእርስዎወቅታዊአድራሻ በ USCIS የተሻሻለመሆኑንለማረጋገጥ ይጠቀሙ፡፡<br><br>uscis.gov/ar-11 |
| **myUSCIS**<br><br>የኢሚግሬሽን ጥቅማ ጥቅሞችን ለማግኘት የሚያስፈልገዉ ማመልከቻ ማስገቢያ ሂደት፣ የዜግነት መብትን ለማግኘት ዝግጅት ለመጀመር የሚረዱ መሳሪያዎች፣ እና ለዜግነት መዘጋጃ ትምህርት ክፍለ ጊዜዎችን ለማግኘት የሚያስፈልጉ አቅርቦቶች እና በአካባቢዎ በሚገኝ ማህበረሰብ ዉስጥ ዶክተሮችን ለማግኘት የሚረዱ ወቅታዊ የሆኑ መረጃዎችን ማግኘት ይችላሉ፡፡ በኦንላይን አካዉንት ላይ በመመዝገብ ማመልከቻን ወይም መጠየቂያን ኦንላይን እንዴት ማስገባት እንደሚቻል እና ስለ እርስዎ ጉዳይ መረጃዎችን ማግኘት ስለሚችሉባቸዉ መንገዶች ይማሩ፡፡<br><br>my.uscis.gov<br><br>myaccount.uscis.dhs.gov |

## ሌሎች የፌደራል አቅርቦቶች

ከዚህ በታች የቀረበዉ ቻርት ለስደተኞች እና ጥገኞች ስለሚሰጡ የፌደራል መንግስት አገልግሎቶች ተጨማሪ መረጃዎችን ይሰጣል፡፡

| የፌደራል መንግስት አቅርቦቶች |
|---|
| **ዩ.ኤስ. ዲፓርትመንት ኦፍ ሄልዝ ኤንድ ሂዉማን ሰርቪስስ ለሕጻናት እና ቤተሰቦች አስተዳደር የስደተኛ ሰፈራ ምደባ ቢሮ (ORR)**<br><br>እርስዎ ስደተኛ ፣ ጥገኛ ፣ እና የስደተኛዉ የቤተሰብ አባል ከሆኑ ፣ በ ORR አማካኝነት እገዛ እና |

## የፌደራል መንግስት አቅርቦቶች

አገልግሎቶች ለመቀበል ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ORR በርካታ ፕሮግራሞች በገንዘብ ይደግፋል እና ያስተዳድራል እነዚህም የገንዘብ እና ሕክምና ድጋፍ፣ የስራ ቅጥር ዝግጅት፣ የስራ ምደባ፣ እና የእንግሊዝኛ ቋንቋ ስልጠና ያካትታሉ፡፡ ከእነዚህ ፕሮግራሞች ዉስጥ አብዛኞቹ በጊዜ-የተገደበ ብቁነት ጊዜ ቆይታዎች አሉዋቸዉ ይህም እርስዎ ጥገኝነት ከተሰጥዎት ወይም ወደ ዩናይትድ ስቴትስ እንደ ስደተኛ ሆነዉ እንዲገቡ ከተፈቀደልዎት ጊዜ አንስቶ የሚጀምር ነዉ፡፡ ***እርስዎ በእነዚህ ፕሮግራሞች የትኛዉም ላይ ፍላጎት ካልዎት ለእነዚህ ፕሮግራሞች ብቁ መሆን አለመሆንዎን በተቻለ ፍጥነት ማረጋገጥ አለብዎት፡፡***

**የግዛቱ ስደተኛ አስተባባሪዎች/የግዛቱ የስደተኞች ጤና አስተባባሪዎች**

acf.hhs.gov/orr/resource/orr-funded-programs-key-contacts

**የግዛቱ ፕሮግራሞች እና አቅርቦቶች**

acf.hhs.gov/orr/state-programs-annual-overview

**የጤና ኢንሹራንስ አቅርቦቶች**

acf.hhs.gov/orr/health

**አቅምን ያገናዘቡ የመኖሪያ ቤት አቅርቦቶች**

acf.hhs.gov/orr/resource/finding-affordable-housing

**የስራ ቅጥር አቅርቦቶች**

acf.hhs.gov/orr/employment-resources

**ዩ.ኤስ. ዲፓርትመንት ኦፍ ስቴት የሕዝብ ቁጥር፣ ስደተኞች፣ እና ስደት ቢሮ ቅበላ እና ምደባ ፕሮግራም**

እርስዎ በዩናይትድ ስቴትስ ዉስጥ የስደተኛ ሁኔታ የፀደቀልዎት ከሆነ፣ እርስዎ ስፖንሰር የተደረጉት በዩ.ኤስ. ዲፓርትመንት ኦፍ ስቴትስ በሚመራ በቅበላ እና ምደባ ፕሮግራም ላይ እየተሳተፈ በሚገኝ የሰፈራ

## የፌደራል መንግስት አቅርቦቶች

ምደባ ኤጀንሲ ነዉ። ስፖንሰር አድራጊዉ ኤጀንሲ በአካባቢዉ ካሉት ቢሮዎች በአንዱ ዉስጥ እርስዎን መመደብ እና የመነሻ አገልግሎቶችን የመስጠት ሀላፊነት አለበት፣ እነዚህም አገልግሎቶች የመኖሪያ ቤት፣ መሰረታዊ የቤት እቃዎች፣ ምግብ፣ አልባሳት፣ ገለጻ መስጠት እና በዩናይትድ ስቴትስ ዉስጥ በሚኖርዎት የመጀመሪያዎቹ ከ 30 እስከ 90 ቀናቶች ዉስጥ ሌሎች ማህበራዊ፣ ሕክምና፣ እና የስራ ቅጥር አገልግሎቶችን ማግኘት እንዲችሉ እገዛ ማድረግን ያካትታሉ። ***እርስዎ መጀመሪያ ላይ እንደ ስደተኛ ዩናይትድ ስቴትስ ሲመጡ፣ የተረጋጋ  ሕይወትን ለመጀመር  እርዳታን ለማግኘት መጀመሪያ ላይ ሊጠይቁ የሚገባዎት የእርስዎ የአካባቢ ሰፈራ ምደባ ኤጀንሲ ነዉ።***

state.gov/refugee-admissions/reception-and-placement

**ዩ.ኤስ. ዲፓርትመንት ኦፍ ስቴት የህዝብ ቁጥር፣ ስደተኞች፣ እና ስደት ቢሮ የባህል ገለጻ አቅርቦት ልዉዉጥ (CORE)**

በዩ.ኤስ. ዲፓርትመንት ኦፍ ስቴት የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግለት፣ CORE ከዩ.ኤስ.-ጋር ለተጣመሩ ስደተኞች በርካታ የባህል ገለጻ አቅርቦቶችን ይሰጣል፡ ፡ ይህ ዌብሳይት በአረብኛ፣ ፋርሲ፣ ኪንያሩዋንዳ፣ ኪስዋሂሊ፣ እና ሶማልኛ ቋንቋዎች የቀረቡ አቅርቦቶችን አካቷል። CORE በዩናይትድ ስቴትስ ዉስጥ ስላለዉ ባህል ገለጻ እንዲያገኙ እርዳታ ያደርግሎታል። ***ስለ ስራ ቅጥር፣ መኖሪያ ቤት፣ ጤና ጥበቃ፣ ገንዘብ አያያዝ የበለጠ ግንዛቤ እንዲኖርዎት እና በዩናይትድ ስቴትስ ዉስጥ የተስተካከለ ሕይወትን ለመምራት የሚያስችሎትን እዉቀት ለማግኘት አሁኑኑ CORE በመጎብኘት ይመርምሩ።***

corenav.org

**ዩ.ኤስ. ዲፓርትመንት ኦፍ ሌበር (DOL)**

DOL የዩናይትድ ስቴትስ ደሞዝ ተከፋዮች፣ ስራ

## የፌደራል መንግስት አቅርቦቶች

ፈላጊዎች፣ እና ጡረተኞችን ደህንነት ያበረታታል፣ ያነቃቃል እና ያሳድጋል፤ ትርፋማ ለሆነ የስራ ቅጥር እድሎችን ለመፍጠር ስራዉን ያከናዉናል፤ እና ከስራ-ጋር የተያያዙ ጥቅማ ጥቅሞች እና መብቶችን ያረጋግጣል፡፡ ***እሰኪ ይህን ይመልከቱ*** *careeronestop.org.* ***በማህበረሰብዎ ዉስጥ ስራዎች እና ስልጠናዎችን ማግኘት እንዲችሉ ይረዳዎታል፡፡***

**የሰራተኞች መብቶች አቅርቦቶች**

dol.gov

**የአሜሪካ ስራ ማእከሎች (በ DOL ስፖንሰር የተደረገ)**

careeronestop.org

877-US2-JOBS (877-889-5627 (TTY))

**ዩ.ኤስ. ዲፓርትመንት ኦፍ ጀስቲስ ስደተኛ እና ተቀጣሪ መብቶች ክፍል**

የዩ.ኤስ. ዲፓርትመንት ኦፍ ጀስቲስ ስደተኛ እና ተቀጣሪ መብቶች ክፍል የስደተኛ እና ዜግነት ድንጋጌ ፀረ-መድልዎ አንቀጽን ተግባራዊ ያደርጋል፡፡ ይህ ደንብ የስራ ቀጣሪዎች በዜግነት ሁኔታ እና የዜግነት መነሻ ላይ በመመስረት ስራ በሚቀጥሩበት፣ ከስራ በሚያሰናብቱበት፣ ወይም በሚመለምሉበት ወይም ለክፍያዎች በሚጠቁሙበት ወቅት መድልዎ እንዳያደርጉ ይከለክላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪም ተቀጣሪዎች ፍትሃዊ ያልሆነ የተለዩ ማስረጃዎችን እንዲያቀርቡ የመጠየቅ ልምምዶች እና በቀል ወይም ማስፈራራት ሁኔታንም ይከለክላል፡፡***እርሰዎ ስራ ለመቀጠር በሚሞክሩበት ወቅት ወይም አሁን ላይ በሚሰሩበት መስሪያ ቦታ ላይ ከመጡበት ሀገር ጋር በተያያዘ፣ ወይም ጥገኛ ወይም ስደተኛ ስለሆኑ ፍትሃዊ ባልሆነ መልኩ ተስተናግጃለሁ ብለዉ ካሰቡ፣ የስደተኞች እና ተቀጣሪዎች መብቶች ከፈፍል እርዳታ ሊሰጥዎት ይችል ይሆናል፡፡***

በዜግነት ወይም ኢሚግሬሽን ሁኔታ ላይ ተመስርተዉ ስለሚደርስ የስራ ቅጥር መድልዎች ላይ የሚያተኩሩ አቅርቦቶች

## የፌደራል መንግስት አቅርቦቶች

justice.gov/crt/immigrant-and-employee-rights-section

800-255-7688 (800-237-2515 (TTY))

***ሶሻል ሴኩሪቲ አስተዳደር***

ስራ ለመቀጠር፣ የሶሻል ሴኩሪቲ ጥቅማ ጥቅሞችን ለመቀበል፣ እና ለሌሎች የመንግስት አገልግሎቶች ማመልከቻ ለማስገባት ሶሻል ሴኩሪቲ ቁጥርእንዲኖርዎት ያስፈልጋል፡፡ ***እርስዎ የሶሻል ሴኩሪቲ ቁጥር እና ካርድ ማግኘት አለብዎት፡፡ ስደተኞች እና ጥገኞችን የሚመለከት የተለየ መረጃን ለማግኘት ከዚህ በታች ያለዉን ዌብሳይት ይጎብኙ፡፡***

ssa.gov/people/immigrants

800-772-1213 (800-325-0778 (TTY))

*በ USCIS ስደተኞች እና ጥገኞች የእንኳን ደህና መጣቹሂደት ላይ የሚኖሩትን* አብዛኞቹን ምስሎች USCIS ጥቅም ላይ ለማዋል መብቶቹን ገዝቷቸዋል፡ ፡ USCIS እነዚህን ምስሎችን ሌሎችን በማያካትት እና ሊተላለፍ-በማይችል መሰረት ላይ ጥቅም ላይ ለማዋል ፍቃድ ተሰጥቶታል፡፡ ሌሎች ሁሉም በእነዚህ ምስሎች ላይ የሚኖሩ መብቶች፣ ይህም ያለ ምንም ገደብ መጠቀም እና ቅጂ መብቶችን ያካትታል፣ በምስሎቹ ባለቤት ተይዘዉ ይቆያሉ፡፡ እነዚህ ምስሎች ለሕዝብ ይፋ በሆኑ መገኛዎች ዉስጥ አይቀመጡም እና የዚህ ህትመት አካል ሆነዉ ካልቀረቡ በስተቀር ጥቅም ላይ የሚዉሉ አይሆንም፡፡

U.S. Citizenship and Immigration Services

uscis.gov